# በተቀባዩ ዘንድ ዋጋ የማይሰጠው ይቅርታ ለህግ የበላይነት ጠንቅ ነው!

*ሚስባህ*

*ይቅርታ ለእኛ ለኢትዮጵያውያን ትርጉሙ ብዙ ነው፡፡ ይቅርታ ባህላችን፣ ወጋችን መለያችንና ኑሯችን ነው፡፡ የኑሮ ዘይቤያችን በራሱ እርስ በርስ የሚየገናኘን፣ የሚያወዳጀን የዝምድና ሰንሰለታችንን በየምክንያቱ የሚያራዝም ነው፡፡ አብሮ መኖር፣ አብሮ መስራት ብዙ እጅግ በጣም ብዙ ነገር አብሮ ማድረግ የኢትዮጵያውያን መለያ ነው፡፡ ብዙ ነገር አብሮ ሲከናወን ደግሞ ልዩነት፣ ቅያሜና ኩርፍያም አብረው መምጣቸው አይቀሬ ነው፡፡*

*ይህን ቅያሜና ልዩነት ከምንፈታባቸው መንገዶች መካከል ቀዳሚውን ቦታ የሚይዘው ደግሞ ይቅርታ ነው። በይቅርታ የማይሸነፍ ወይ የማይለወጥ አዕምሮ በሀገራችን ማኅበረሰብ ውስጥ ማግኘት ይከብዳል፡፡*

*ታዲያ ይቅርታው ራሱን የቻለ ቅድመ ሁኔታና የአፈፃፀም መንገድ እንዳለውም መረሳት የለበትም፡፡ ለይቅርታ ጠያቂዎች ሁሉ ጥፋትን ማመን የመጀመሪያው ተግባር ነው፡፡ ከዚያም መልዕክተኛ መላክ፣ መደራደርና ይቅር መባባል፣ ደግሞ እንደገና በይቅርታ የታደሰ አዲስ ግንኙነት መፍጠርና ወደ ቀድሞው ወዳጅነት መመለስ፤ ተደጋጋሚ ጥፋት እና ተደጋጋሚ ይቅርታ በባህላችን ፀያፍ ነው፡፡*

*በላይ በላዩ የሚያጠፋ በዳይ የሚሸመግለው አያገኝም። ቢያገኝም ተበዳዩ እንደ መጀመሪያው ልቡ የነፃ አይሆንም፣ ተጠራጣሪ ይሆናል፡፡ የቀደመውን ግንኙነት ዳግም ለመመሥረት ወኔ ያጣል፤ አይቻለውምም፡፡ በተደጋጋሚ ይቅርታ የተነሳ አስታራቂ ሽምጋይ ከመሆኑ ይልቅ ፌዘኛ ይሆናል፡፡ በዳይም በማይታይ ህገ ልቦና ከማኅበረሰቡ ይነጠላል፡፡ እኛ እንዲህ ነን፡፡*

*ይቅርታችን ወዝ ያለው ነው፡፡ አብሮን ለዘመናት ኖሯል፡፡ የኃይማኖቶቻችን መሠረትም በመሆኑ ትልቅ ዋጋ ያለው እንጂ እንዳሻን የምናነሳውና እንደፈለገን የምንጥለው አይደለም፡፡ ስለይቅርታና ባህላችን ብዙ መናገር ይቻላል፡፡ ለመንደርደር ያህል ግን በቂ ይመስለኛል፡፡*

*አሁን ወደ ጉዳዬ ስመጣ መንግሥትና ለዛ የለሹን ይቅርታ በተመለከተ ያለኝን ሥጋት አወሳለሁ፡፡ የሥጋቴ መነሻ የአሜሪካ ድምጽ ራዲዮ አማርኛው አገልግሎት የካቲት 22 ቀን 2004 ዓ.ም አየር ላይ ያዋለው ዘገባ ነው፡፡ "በኢትዮጵያ በእሥር ላይ የሚገኙትን ሁለት የስዊዲን ጋዜጠኞችን የማስለቀቁ ድርድር እየተጠናቀቀ ነው" ይላል በዐቢይ ርዕስነት የቀረበው የእለቱ ዘገባ፡፡*

ድርድሩ ስለመጠናቀቁ ተናገሩ የተባሉትና ዘገባው በምንጭነት የጠቀሳቸው ደግሞ የቀድሞው የቤልጅየም የውጭ ጉዳይ ሚኒስትርና የአውሮፓ ፓርላማ አባል የሆኑት ሊዊስ ሚሼል ናቸው፡፡ ሊዊስ ሚሼል ታሳሪዎቹን በግል እንደጎበኙና በታሳሪዎቹ የወቅቱ ሁኔታ እንዲሁም በፀፀት ስሜታቸው እንደተደሰቱ መናገራቸውን የገለፀው ዘገባ ጋዜጠኞቹ ትልቅ ስህተት ፈጽመናል ሲሉ መፀፀታቸውንና ይቅርታ ለመጠየቅ ዝግጁ መሆናቸውን እንደነገሯቸውም ጭምር አትቷል፡፡

ይህ ብቻ አይደለም፡፡ የእለቱ ዐቢይ ርዕስ ከሊዊስ ሚሼል በተጨማሪ የሲውዲኑ ጠቅላይ ሚኒስትር ፍሬድሪክ ሬይንፌልትም ከጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ጋር ተገናኝተው በጉዳዩ ዙሪያ መነጋገራቸውን ዘገባው ጨምሮ አመልክቷል፡፡

ተቀባዩ ተገቢውን ክብር የማይሰጠውና ከልቡ ላልተጸጸተበት ስህተት የሚሰጥ ይቅርታ ለእኔ የህግ የበላይነትን ለአደጋ የሚዳርግ አዝማሚያው ነው፡፡ ለምን ቢባል ፀቤ ይቅርታ ከመጠየቅና ይቅርታን ከማድረግ የተቀደሰ ተግባር ጋር አይደለም፡፡ ፀቤ የይቅርታው ጥያቄና ድርድሩ፣ አደራዳሪዎቹና የጉዳዩ ክብደት እንዲሁም ቀደም ብለው ከተከናወኑ የይቅርታ ሂደቶች ጋር የተያያዘ ነው፡፡ እነዚህን ነጥቦች ዘርዘር አድርገን ለማየት ስለይቅርታ ህግና የአፈፃፀም ሂደት በተመለከተ አዋጃችንን እና ህገ መንግሥታችንን መፈታተሽ ጠቃሚ ይሆናል፡፡

በዓለም ላይ ባሉ ሀገሮች ሁሉ ማለት ይቻላል፤በአሁኑ ጊዜ “ይቅርታ” የህግ ሥርዓት ተበጅቶለት ተግባራዊ በመደረግ ላይ ይገኛል፡፡ በመደበኛው ህግና በህግ ተርጓሚው አካል መካከል የሚፈጠሩ ክፍተቶችን ለመሙላት ወይም በተለያዩ ምክንያቶች የሚፈጠሩ የውሣኔ አሰጣጥ ስህተቶችን ለማረምና ለማስተካከል “ይቅርታ” ህግ ወጥቶለት ተግባራዊ በመደረግ ላይ እንደሚገኝ ከኢፌዴሪ የፍትህ ሚኒስቴር ያገኘሁት መረጃ ያረጋግጣል፡፡

ምንም እንኳን ራሱን የቻለ የይቅርታ ህግ ተቀርፆ የተሰራበት ጊዜ ባይኖርም በተለያዩ ህጎች ውስጥ በማስገባት ይቅርታ በሀገራችን ተግባራዊ ሲደረግ መቆየቱን የሚያመለክተው ይህ መረጃ በኢትዮጵያ ከመጀመሪያውና ከ1931 ዓ.ም ጀምሮ የነበሩት ህገ መንግሥታት ይቅርታን በተመለከተ ድንጋጌዎችን ይዘው መውጣታቸውን ያመለክታል፡፡

ከህገ መንግሥታቱ በተጨማሪ በወንጀለኛ መቅጫ ህጉም የይቅርታ ድንጋጌዎች ተካተው ይገኛሉ፡፡ ከ1987 ዓ.ም ወዲህም ሀገራችን ፌዴራላዊ የመንግሥት አወቃቀር የምትከተል እንደመሆኗ በፌዴራልም ሆነ በክልሎች ህገ መንግሥታት ውስጥ ይቅርታን የሚመለከት ድንጋጌ ተካቶ ወጥቷል፡፡

ይህንኑ የፌደራልና የክልሎች ህገ መንግሥታት ተከትሎ በፌዴራል ደረጃ የይቅርታ ሥነ ሥርዓት አዋጅ ቁጥር 395/1996 ወጥቶ ተግባራዊ እየተደረገ ነው፡፡ ከአፋር ክልል በስተቀር በሁሉም ክልሎች የይቅርታ ሥነ ሥርዓት አዋጅ ወጥቶ ተግባራዊ በመደረግ ላይ የሚገኝ መሆኑን ሙሉጌታ አያሌው ጥቅምት 2004 ዓ.ም ላይ “የይቅርታ አሰጣጥ ሁኔታ በኢትዮጵያ” በሚለው ጥናታቸው ላይ አስቀምጠዋል፡፡

ወደ ይቅርታ ትርጓሜ ስንመጣ በተለያየ መልኩ በቀረቡ ጽሁፎች የተለያየ አገላለጽ እየተጠቀሙ ቢተረጉሙትም በያዙት ደረጃ ሁሉም ተመሣሣይ ሆነው አግኝቻቸዋለሁ፡፡

በወንጀል ድርጊት ምክንያት የተላለፈ ቅጣትን የሚያቀል ወይም እስከ መጨረሻው የሚያስቀር በአስፈፃሚው አካል የሚወሰድ አስተዳደራዊ እርምጃ ነው በሚል ብላክስ ሎው (Blaks Law) የተሰኘ የእንግሊዝኛ የህግ መዝገበ ቃላት የተረጎመው ነው፡፡ ዊኪፒዲያ (wikipedia) የተሰኘው ሌላው የህግ መዝገበ ቃላት ደግሞ "ለአንድ የተፈፀመ ወንጀል እና ይህን ወንጀል ምክንያት አድርጎ ለተሰጠ ቅጣት ይቅር ማለት ነው" በሚል ከብላክ ሎው አንፃር መሠረታዊ የሆነ የይዘት ልዩነት ሳይሰጥ ይተረጉመዋል፡፡

እነዚህን ትርጓሜዎች በሀገራችን ይቅርታን አስመልክቶ ለመጀመሪያ ጊዜ ከተደነገገው የይቅርታ አሰጣጥ ሥነ ሥርዓት አዋጅ ቁጥር 395/1996 አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ ትርጓሜ ጋር ስናስተያያቸው ትርጉማቸው ሙሉ ለሙሉ በሚባል ደረጃ ተመሣሣይ ሆነው እናገኛቸዋለን፡፡ "የይቅርታ ጥያቄ " ማለት አንድ ፍርድ በሙሉ ወይም በከፊል ቀሪ እንዲሆን ወይም የቅጣቱ አፈጻጸም እና ዓይነቱ በቀላል ሁኔታ እንዲፈፀም የሚቀርብ ጥያቄ ነው" ይለዋል አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 4፡፡

ስለ ይቅርታ ትርጉምና መነሻዎች ይህቺን ታህል ካወራን አጀንዳችን ለዛ ያጣ ይቅርታና የህግ የበላይነትን የተመለከተ በመሆኑ የይቅርታ ዓላማን በተመለከተ ደግሞ ጥቂት ነገር ማለት ግድ ይለናል፡፡ ማንኛውም ህግ የሚወጣው አንድን ዓላማ ለማሳካት መሆኑ ግልጽ ነው። የይቅርታ ህግም የሚወጣው እንደዚሁ አንድን ዓላማ ለማሳት ታስቦ ነው።

ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው በህግና በህግ ተርጓሚው በኩል የሚፈጠሩ ክፍተቶችን ለመሙላት ታስቦ የይቅርታ ህግ የሚወጣ ቢሆንም በሌላ መልኩ ምንም እንኳን ዋና ዓላማ ተደርጎ ባይወሰድም የታራሚዎችን መጨናነቅ በመቀነስ ረገድ ይቅርታ አስተዋጽኦ የሚያደርግ መሆኑ እሙን ነው።

በአጠቃላይ የይቅርታ ዓላማ የኅብረተሰቡን ደህንነትና ጥቅም ማስከበር መሆኑ በይቅርታ ሥነ ሥርዓት አዋጅ ቁጥር 395/1996 አንቀጽ 11 ላይ በግልጽ ተመልክቷል። ከዚህ መረዳት የሚቻለው ደግሞ የህዝብ ጥቅምና ደህነነት እስከተከበረ ጊዜ ድረስ ብቻ ይቅርታ መሰጠት ያለበት መሆኑን ነው። በሌላ መልኩ የህዝብ ጥቅምና ደህንነት የሚጎዳ ከሆነ ይቅርታ ሊደረግ አይገባም ማለት ነው ።

የህዝብ ጥቅምና ደህንነት መከበር ሲባል ምን ማለት ነው? መለኪያውስ ምንድ ነው? የሚሉትን ጥያቄዎች በተመለከተ አዋጁ በግልጽ ያስቀመጠው ነገር ባይኖርም የሰው ዘር ማጥፋት፣ ያለፍርድ የሞት ቅጣት እርምጃ መወሰድ፣ አስገድዶ ሰውን መሰወር ወይም ኢ ሰብዓዊ ድርጊቶችን መፈፀም ይቅርታ የሚያስከለክሉ መሠረታዊ ጉዳዮች እንደሆኑ ከላይ በተጠቀሰው አዋጅ አንቀጽ 28 (1) ተመልክቷል።

ይቅርታ በህግ፣ በሣይንስ፣ በባህልም ሆነ በወጋችን ይህ ከሆነ ዘንዳ አሁን ለዛ ያጣው የመንግሥታችን ይቅርታ መልስ ያገኘ ይመስለኛል። ምክንያቱ ደግሞ ያለአግባብ ከአዋጁ ውጪ በሆነ ምክንያት የሚሰጥ ይቅርታ ለህግ የበላይነት ጠስ በመሆኑ።

የስዊድን ጋዜጠኞችን በተመለከተ ከላይ ከተገለፀው የይቅርታ አሰጣጥ ዓላማ አንፃር እንፈትሸው እስኪ፦ እነኚህ ጋዜጠኞች ሉዓላዊነታችንን ተዳፍረው በህገ ወጥ መንገድ ሀገራችን ውስጥ መገኘታቸው የመጀመሪያው ወንጀል ነው። ሲቀጥል በጋዜጠኝነት መታወቂያ መቅረጸ ድምጽ ሳይሆን የጦር መሣሪያ ይዘው መገኘታቸው ሁለተኛው ወንጀል ነው። ሦስተኛውና ትልቁ ወንጀል ደግሞ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አሸባሪ ናቸው ሲል ከፈረጃቸው ጋር በመሆን የህዝብን ደህንነትና ጥቅም በሚጎዳ ተግባር ላይ ተሰማርተው መገኘታቸው ነው።

ከዚህ በመነሳት ስዊድናውያኑ በሀገራቸው ይህ ዓይነት ሁኔታ ቢፈጠር የማያደርጉትን በሀገራችን የተፈፀመውን ወንጀል ወደ ጎን በመተው ለጋዜጠኞቹ ይቅርታ ይደረግ ዘንድ መታተራቸው ለእኔ ከምንም በላይ ለሀገራችን ያላቸውን ንቀት የሚያመለክት ነው።

ይህ ብቻ አይደለም፡፡ ከሚሰጡት ጋዜጣዊ መግለጫና ቀደም ብዬ ካሰፈርኩት የአሜሪካ ድምጽ ራዲዮ የአማርኛው አገልገሎት ዘገባ እንደተረዳሁት የይቅርታ አሰጣጥ ህጉን ታሳቢ ባላደረገ መልኩ ከጠቅላይ ሚኒስትራችን ጋር ብቻ በጎን መደራደራቸውን የሚያመለክትና ድርድራቸውም ውጤታማ ሊሆን እንደሚችል የሚያሳይ ነው።

በእኔ በኩል የስዊድን መንግሥት እንደሚለውና የሰብዓዊ መብት ጠባቂ ነን የሚሉ ተቋማት እንደሚያወጡት መግለጫ ለነዚህ ሰዎች መንግሥታችን ይቅርታ የሚሰጥ ከሆነ በአዋጁ እንደሰፈረው ይቅርታ የሚያስከለክለውን ህግ መጣስና ጉዳት ሊደርስበት የነበረውን ህዝብ መናቅ ነው። በተለይ ከምርጫ 97 በኋላ መንግሥት እየሰጠ የሚገኘው ይቅርታ ከአዋጁ ጋር እጅግ የተጣረሱ መሆኑ ሳያሳምመው ዛሬ ደግሞ ለነዚህ ጋዜጠኞች ይቅርታ ቢያደርግ ይቅርታው ለዛ ከማጣትም ባሻገር በመንግሥት ላይ ያለንን አመኔታ የሚሸረሽር ነው።

አንድ ጨዋታ የሚመስል ነገር ግን እውነትና መንግሥት ምን ያህል ለይቅርታ ያለው ግምት እየወረደ ስለመምጣቱ የሚያመላክት ሰሞንኛ ገጠመኜን እዚህ ጋር ባነሳ ጥሩ ይመስለኛል።

አንድ ነጋዴ የሆነ ባልንጀራዬ ባልንጀራው በእሱ የሂሳብ መዝገብና የንግድ መለያ ቁጥር በድብቅ ሲነግድ እንዳገኘውና ይህም የመንግሥት ባለዕዳና ተጠያቂ የሚያደርገው መሆኑን ያጫውተኝና ይህንኑ የባልንጀራውን የሌብነት ተግባር ለሚመለከተው አካል ለማጋለጥ እየተንቀሳቀሰ መሆኑን ይገልጽልኛል። ከሣምንት በኋላ እንዴት ሆነልህ? ስለው አታላዩ በህግ ቁጥጥር ሥር እንደዋለ ነግሮኝ እሱ ባላወቀው ምክንያት ግን ወዲያው በመለቀቁ ማዘኑን አጫወተኝ። ግለሰቡን በግል አላገኘኸውም ወይ? የሚል ጥያቄ አስከተልኩ ‘አግኝቼዋለሁ’ አለኝ። ታዲያስ ምን ሆኜ ነው ይህን ፀያፍ የማታለል ተግባር የፈፀምኩት አለህ ቀጠለ ጥያቄዬ እሱማ ምን ይላል ደግሞስ ምን ያድርግ ይህን ያህል በእኔ ላይ በደል መፈፀሙና መንግሥትን ለኪሳራ መዳረጉ ቅንጣት ታህል ሳይቆጨው ተሳስቼ ነው “ይቅርታ አድርግልኝ" አለኝ። ምን ያድርገው ያልኩህ መንግሥትም ለትንሽ ለትልቁ ይቅርታ ማለትን መለያ ምልክቱ /Trade mark/ በማድረጉ ባልንጀራዬስ ከማን ይማር ብዬ ነው አለኝ፡፡ አያችሁት ጨዋታ የሚመስለውን ግን ሰሞኑን የተከናወነ ድርጊት። ለእኔ ያሳፍራል።

ደግሞ ሌላ፦ የፍትህ አምደኛው ፕሮፌሰር መሥፍን ወልደማርያም ልክ እንደለመዱት የሲዊድን ጋዜጠኞች አሸባሪ አይደሉም ነፃ አውጪ እንጂ ብለው ሰሞኑን አስነብበውናል፤ ነፃ ወጪዎቹ ደግሞ ፕሮፌሰሩ እንደሚሉት እኛ ነን። እኚህ ሰው እያደር እየባሰባቸው ነው ከማለት ሌላ ምን እንደምላቸው አላውቅም። አሁንም የለመደ እንዲሉ ይቅርታ ይደረግላቸው ብለው እየሞገቱ ነው። መንግሥት ይቅርታ ያላደረገ እንደሆነ መዋረዱ ነው ሲሉም ያስጠነቅቃሉ። ስለመዋረዱ ያቀረቡት ምክንያት ግን ኢ. ተጠየቃዊ እና ለዛ ቢስ ነው።

የማስተላልፈው መልእክት እባካችሁ ግለሰቦችም ሆናችሁ እንደግል፣ መንግስትም ሆናችሁ እንደመንግስት አታሳፍሩን የይቅርታን ክብደት  አታሳንሱብን።